

# አቶ ኃይለሥላሴ ገብራይ ማን ነበሩ?

የሰው ልጅ እዚህ ዓለም በሚመጣበት ጊዜ የሚያከናውናቸው ተግባራት አሉት። ከነዚህም ውስጥ የራሱንና የቤተ-ሰቡን ኑሮ ለመደጎም የሚያደርገው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ አንዱ ነው። ይህንን ግዴታውን በተገቢ መንገድ ለመወጣት መቻል በራሱ የሚመሰገን መሆኑ መዘንጋት የሌለበት መሆኑን ብንገነዘብም፤ ከራሳቸውና ከቤተሰባቸው ሕይወት አልፈው ለሌላ ወገናቸው ደህንነት ሲሉ ያላቸውን የሚሰጡ መኖራቸውን ስንታዘብ ደግሞ ይበልጥ ሊመሰገኑና ሊወደሱ የሚገባቸው የሰው ልጆች እንዳሉ እንረዳለን። ዛሬ በዚች አጭር ማስታወሻ የምንዘክራቸው አባትም ከነዚህ በመልካም ምግባራቸው ከሚታወቁት አዛውን አባቶች አንዱ ናቸው። እኚህ ዛሬ በመልኻም ምግባራቸው የምንዘክራቸው አባት አቶ ኃይለሥላሴ ይባላሉ።

አቶ ኃይለሥላሴ ገብራይ ወልደሥላሴ ከኣባታቸው ከአቶ ገብራይ ወልደሥላሴና ከእናታቸው ከወይዘሮ መድህን ወልዱ በምሥራቃዊ ሰሜን ትግራይ በኢሮብ ወረዳ ልዩ ስሟ ኣዎ በምትባል መንደር ውስጥ ሓምሌ 1914 ዓ.ም. ነበር የተወለዱት።

አቶ ኃይለሥላሴ በተወለዱበት አከባቢ ትምህርት-ቤት ስላልነበረ ማንበብንና መፃፍን የተማሩት በቤታቸው ውስጥ በአባታቸው ነበር። በኋላ ግን በዓዲግራት ጎልዓ በምትባል ክፍለ ከተማ ውስጥ በነበረው ላዛርስት ሚሲዮን የካቶሊክ ትምህርት-ቤት ውስጥ ትምህርታቸውን ለመከታተል ችኋል።

አቶ ኃይለሥላሴ በ1936 ዓ. ም. በኢትዮጵያ መከላከያ ውስጥ ገብተው በጉምሩክ መሥርያ-ቤት ተቀጥረው ሠርቷል። በኋላም ከወታደርነት ወጥተው በኢትዮጵያ ገንዘብ ምኒስቴር መሥርያ-ቤት ተቀጥረው መጀመርያ በሰነድ ያዥነት፣ ቀጥሎም በመቐለ ከተማ የሚኒስትሩ መሥርያ-ቤት የፋይናነስ

ጉዳይ ሓላፊ በመሆን ሠርቷል። በኋላ ደግሞ በነበራቸው ሙያ አዲስ አበባ ውስጥ በፋይናንስ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ተቀጥረው መጀመርያ የመሥርያቤቱ የፋይናነስ ሹም በመሆን፣ በኋላም የሸዋ ክፍለ-ሃገር የፋይናንስ ወኪል በመሆን ከመንግሥት ሥራ ጥሮታ እስከገቡበት ቀን ድረስ ሠርቷል።

አቶ ኃይለሥላሴ የረጂም ጊዜ ባለቤታቸው ከነበሩት ከወይዘሮ ተብርህ ወልደዮሓንስ ዲኒ ጋር ትዳር መስርተው፤ 11 ልጆችን ወልደዋል።

አቶ ኃይለሥላሴ ከመንግስት ሥራ ጥሮታ ከወጡ በኋላም የካቶሊክ ቤተ-ክርስተያን የአዲሰ አበባ ሃገረ-ስብከት የፋይናስ ጉዳይ ሓለፊ ሆነው ለጂም ጊዜ ሠርቷል። ከዚህም ሌላ አቶ ኃይለሥላሴ በሠሩበት ሁሉ የተመሠከረላቸው ታማኝና በሃይማኖተዊ እምነታቸውም ጠንካራ ሰው ነበሩ።

ከሁሉም በላይ አቶ ኃይለሥላሴ የወጡበት የኢሮብ ህዝብ ታሪክና ባህል እውቅና እንዲያገኝ በጽሑፍና በተለያዩ ሰብሰባዎች ባደረጉት ንግግሮች ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሰው ነበሩ። በ1990 የኢሮብ አከባቢ በኤርትራ ጦር ሓይል የተወረረበት ጊዜ "የኢሮብ ህዝብ የኢትዮጵያ አካል ያለሆነበት ጊዜ የለም" በሚል አርእስትና "የተወረረው መሬትና ህዝብ/ኢሮብ" በሚል አርእሰት በአዲስ አበባ የወጡ መግለጫወች ደራሲዎች አንዱ እንደነበሩ ይታመናል።

አቶ ኃይለሥላሴ "ማርያም ዓሊተና የኢሮብ ማሕበር" በማቋቋም በአዲስ አበባ አከባቢ የሚኖሩ የኢሮብ ተወላጆች ተደራጅተው እንዲረዳዱ አድርገዋል። ማህበሩ ያኔ በነበረ የፖለቲካ ሁናቴ ምክንያት (የዓሊተና አከባቢ ወታደራዊ ደርግን በሚቃወሙ ሽማቂ ሓይሎች ቍጥጥር ሥር ስለነበረ ለአባሎች ድህንነት ሲባል) "የማርያም ማህበር" በሚል ስያሜ ነበር የሚታወቀው። አቶ ኃይለሥላሴ ባለፈው ኅዳር ወር በ92 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለዩበት ጊዜ ድረስ ማህበሩ እንዳይፈርስ ኢሮቦች እንዲተባበሩ አባታዊ ምክር እየሰጡ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ሁሉ የኢሮብ ህዝብ ጠበቃ በመሆን የመጡበት ማኅበረ-ሰብ ልሳን ሆኖው እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ በታማኝነትና ቅንነት ሲያገለግሉ ኖሮዋል።

አቶ ኃይለሥላሴ በተሰጣቸው ጊዜ ከሚጠበቀው በላይ ለሃገርና ለወገን ሠርተው አልፈዋል። ስማቸው በኢሮብ ህብረተስብ፣ በአዲስ አበባ የካቶሊክ ሃገረ-ስብከትና በሚያውቋቸው ዘንድ ሁሉ ህያው ሆኖ ይኖራል። መልካም ምግባራቸውም በኢሮብ ህዝብ ዘንድ በመልካም ሲታወስ ይኖራል።

የካቲት 2006 ዓ.ም

ከኢሮብ ማብሎ ድረ-ገጽ